የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄን
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy

ቀን ሰኔ 7 2000

# የመለስ አምባገነን አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚያደርሰውን አሰቃቂ ግፍና እልቂት የግንቦት7 ንቅናቄ እጥብቆ ያወግዛል።

በማያሻማ ቋንቋና በማያሻማ ማስረጃ ደግፎ፣ የታወቀው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት፣ ህዩማን ራይት ወች፣ የመለስ አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የፈጸመውን የግፍ ወንጀል ከትናንብት በስተያ ሰኔ 4 2000 ዓ.ም ባወጣው ዘገባ አጋልጦታል።

በርካታ መንደሮች በቃጠሎ እንዳልነበሩ ተደርገው ወድመዋል። ህጻናት፣ ኣዛውንቶች ሴቶች፣ ወንዶች አቅመ ደካሞች በሙሉ በመለስ ዜናዊ ጦር አሰቃቂ የጅምላ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋል። ሴቶችን እያስገደዱ አስነዋሪ በሆነ መንገድ መድፈር፣ ዘረፋ፣ ማፈናቀልና ማሳደድ ከጭፍጨፋው ጋር በተጓዳኝ እየተፈጸመ ያለ ግፍ ነው። ይህ ወንጀል መለስ ዜናዊና የግፍ ተባባሪ ጓደኞቹን በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰትና በሰብአዊነት ላይ በተፈፀመ ከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቃቸው እንደሆነ የሰብአዊ መብት ተሟገቹ ቡድን በግልጽ አስቀምጦታል።

ይህ አይነቱ አሰቃቂ ወንጀል በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ መፈጸም ከጀመረ አመታት አልፏል። አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና በሰብአዊነት ላይ የተደረጉ ከፍተኛ ወንጀሎች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ የጅምላ ጭፍጨፋዎችና የዘር ማጥፋት እርምጃዎች በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በአፋር፣ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞችና ክልሎች የመለስ አገዛዝ ሲፈጽም እንደነበርና አሁንም እየፈጸመ እንደሆነ ይታወቃል።

ይህ በሁሉም የሃገራችን ክልሎች በሁሉም ህዝብ ላይ የመለስ አገዛዝ የሚያወርደው የመከራ ዝናብ ሁላችንንም በጋራ የሚያቃጥል ሆኖ ሳለ፣ አስካሁን እንደታየው ሁላችንም በጋራ በእዚህ መከራ አምራች በሆነ አገዛዝ ላይ በጋራ ተባብረን እንዳንነሳ ሆነናል። የዚህ ዋንኛው ምክንያት ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ እንዲያመቸው በመሃከላችን የሚያሰራጨው ዘረኛ አመለካከትና የዘረጋው መተባበርና መተሳሰብን ባይተዋር ያደረገ ዘረኛ የፖለቲካ ስርአት ነው።

ሁሉችንም የሃገሪቱ ዜጎች የምንገኝበትን ፈታኝና አሰቃቂ ሁኔታ ማሸነፍ የምንችለው መለስ ዜናዊ ያደራጀውን ግፍ ፈጻሚ ሰራዊትና የስለላ ሃይል፣ የሚያሰራጨውን የከፋፍሎ መግዣ መርዘኛ አመለካከት፣ የአንዱን ዜጋ ጥቃት የሁሉም ዜጋ ጥቃት፣ የአንዱን ክልል ህዝብ ጥቃት፣ የሌላው ክልል ህዝብ ጥቃት፣ አድርጎ በሚያይ የጋራ ተቆርቋሪነት እርስ በእርሳችን ስንቆላለፍ ብቻ ነው።

ይህ የመቆላለፍ እርምጃ ዛሬ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን የሚሰቀጥጥ እርምጃ በአንድ ድምጽ በማውገዝ ይጀመራል። የኦጋዴን ወገኖቻችን ራሳቸውን እንዲህ አይነቱን ግፍ ለመከላከል በሚያደርጉት ትግል ከጎናቸው መቆማችንን በተግባር ስናረጋግጥ የጋራ ተቆርቋሪነታችን እውን ይሆናል።

ግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በቅድሚያ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል ይኮንናል። የኦጋዴን ወገኖቻችን የመለስ ዜናዊን አስከፊና አጸያፊ ጭፍጨፋ

ለመመከት የሚያደርጉትን ትግል አቅሙ በፈቀደው በማናቸውም መንገድ ለመርዳት ዝግጁ መሆኑን ያስታውቃል።

በሌላ በኩልም፣ በሃገራችን ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰባትና ሌሎችም ተቋማትና ግለሰቦች በሁሉም የሃገራችን ዜጎች ላይ የሚፈጸምን በደል በደላቸው አድርገው ማየት፣ ይህንን እንዲቆም መንቀሳቀስ የኢትዮጵያዊነት የዜግነት ግዴታ እንደሆነ ተረድተው በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እንዲያወግዙ፣ ይህ ግፍ አንዲቆም የሚችሉትን እንዲያደርጉ ግንቦት7 ጥሪ ያቀርባል።

ወደፊትም ቢሆን በየትኛውም የሃገሪቱ ክልል፣ በየትኛውም የሃገሪቱ ዜጋ ላይ የሚፈጸምን ግፍና ወንጀል ሁላችንም የሃገሪቱ ዜጎች በራሳችን ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል ልንኮንነውና ልንቃወመው የሚያስችል ዝግጁነት ሊኖረን ይገባል። በእንዲህ አይነቱ የመተሳሰብና የመቆርቆር የጋራ ስሜት ብቻ ነው፣ መለስ ዜናዊ ሁላችንም ከፋፍሎ እየረገጠ ለመግዛት፣ ካልሆነለት የሃገራችንን አንድነት በማናጋት ህልውናዋን ለማፍረስ ያውጠነጠነውን አደገኛ ሴራ ማምከን የምንችለው።

የአለም አቀፍ ህብረተሰቡም ለአጭር ግዜ፣ ለጠባብ ጥቅምና ፍላጎት ማስፈጸሚያ ሲል እሹሩሩ የሚለውን የመለስን አገዛዝ በቃህ ሊለው ይገባል። በአፍሪካችን ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ግፈኛ መንግስት በማሞካሸትና አቅም በማጠናከር የሚቀጥሉ የውጭ መንግስታት ድርጊት መቆም አለበት። ውሎ አድሮ እነዚህ ከመለስ ግፈኛ አገዛዝ ጋር ሽርክና የገቡ መንግስታት ይህን ሽርክናቸውን በፍጥነት ካላቋረጡ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ እነሱንም ቢሆን ከወንጀለኛው የመለስ አገዛዝ ለይቶ ማየት ከማይችልበት ደረጃ ላይ እንደሚያደርሱት ሊያውቁት ይገባል። ይህም የአመለካከት ክረት ለኢትየጵያ ህዝብም ሆነ ለእነዚህ የውጭ መንግስታት ዘላቂ ጥቅም የማይበጅ በመሆኑ በተለይ የምእራብ መንግስታት እስካሁን በኢትዮጵያ ላይ ሲያራምዱት የነበረውን ፖሊሲያቸውን በአስቸኳይ ከልሰው የኢትዮጵያ ህዝብ ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል እንዲደግፉ ግንቦት7 ጥሪውን ያቀርባል።

ግንቦት7 ንቅናቄ
የፖለቲካ አመራር